# የሰባት ቀናት
# የልግስና ሙግት

MB FOUNDATION
Giving Meaning to Money®

# የሰባት ቀናት
# የልግስና ሙግት

ልግስና ጽንሰ-ሐሳብ (“ቲዮሪ”) አይደለም። በሰባት ቀናት የልግስና ሙግት ማከናወን የተፈለገው ዋና ነገር እናንተ በደስታ የተሞላና ክርስቶስን ማእከል ያደረገ የልግስና ሕይወት እንዲኖራችሁ ማበረታታት እና ማነቃቃት ነው። አንዳንዶች ይህ ሕይወት ምን ይመስላል በማለት ይጠይቁ ይሆናል? ከተግባር አኳያ ለመጠየቅ ያህል፣ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስን፣ ምሳሌዎችን እና ተዛምዶአዊ ሐሳቦችን ወስደን በሕይወታችን ተግባራዊ የምናደርገው እንዴት ነው?

እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ ይህንን የሰባት ቀናት የልግስና ሙግት በጥንቃቄ እና በአግባቡ እንድትወስዱ እናሳስባለን። በሳባቱ ቀናት ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ቀን የመጽፍ ቅዱስ ክፍለ ምንባብ፣ ትምህርት እና ሙግት (challenge) ተካቷል። በእያንዳንዱ ሙግት ዙርያ ተጨማሪ ማንበብ እና ማጥናት ከፈለጋችሁ ይረዳችሁ ዘንድ ከአብዛኛዎቹ ሙግቶች ጋር የዋቤ መጻሕፍት ዝርዝር ቀርቧል።

ስትደርሱበት እንደምትመለከቱት ይህንን የሰባት ቀናት ሙግት መውሰድ ነጻነት፣ እምነት፣ ብርታት፣ ተግባር፣ ዝግጁነት፣ ለውጥ እና ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል ወይም ኀላፊነት ለመውሰድ መዘጋጀትን ያካትታል። በመጨረሻ ግላዊ የሕይወት ለውጥ እንደሚያመጣም እናምናለን።

ይህንን ሙግት ለመውሰድ ዛሬ ራሳችሁን ስጡ፤ እነዚህን መርህዎች በሕይወታችሁ ተግባራዊ ለማድረግ አንድ ሳምንት ለይታችሁ ወስኑ። ውጤቱ የተሻለ ለጋስ መሆን ብቻ ሳይሆን ታላቁን ሰጪ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ የሚመነጭ ልዩ ደስታ ማግኘትም ጭምር እንደ ሆነ እናውቃለን።

# ቀን አንድ

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባለ ዐደራነት፤ የለጋስነት ሁሉ መሠረት

BY DR. ZENET MARAMARA (PHILIPPINES)

---

**የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍል**

“ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።” (መዝሙር 24÷1)

**ትምህርት**

መዝሙረኛው በግልጽ እንደሚያውጀው የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር የፍጥረታት እና በውስጥዋ ያሉት ሁሉ ባለ ቤት ነው። በመልካምነት የምድርን በረከት ሁሉ እንድንጠቀምበት እና እንድንደሰትበት ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ ባለ ቤትነትን በፍጹም ለሰዎች አላስተላለፈም። የእርሱ ባለ ቤትነት ቀጥሏል፤ እኛ የእርሱ ባለ ዐደራዎች ነን። ይህ እውነት ለምንኖረው ሕይወት እና የተሰጠንን ንብረት (ገንዘብ፣ ያለን ንብረት ሁሉ፣ ሥራችን፣ ንግዳችን፣ እና ያለን ሁሉ በዚህ ውስጥ ይካተታል) ለምንጠቀምበት መንገድ ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ የማይችል ታላቅ ተዛምዶ አለው።

እግዚአብሔር ባለ ቤት፣ እኛ ደግሞ ባለ ዐደራዎች ከሆንን የባለ ቤቱን ፈቃድና ፍላጎት ልንከተል ይገባል። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ልብ ማወቅ፣ ለፈቃዱ ራስን መስጠት እና ለተጠራንበት ዓላማ መኖርን ያካትታል። የእግዚአብሔርን ፍጥረታት እና እርሱ የሰጠንን ሐብት እንደ ባለ ዐደራ መያዝ/መጠቀም ማለት የምንቀበለውን የትኛውንም በረከት ለሌሎች ማካፈል ማለት ነው። ልግስና በየዕለቱ በነጻ፣ አትረፍርፎ ለሚባርከን ለእግዚአብሔር አንደ ባለ ዐደራ የምንሰጠው የምስጋና ምላሽ ነው። እግዚአብሔር ለግል ፍላጎታችን በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ይባርከናል፤ እኛም ከእርሱ በተቀበልነው በረከት ለኑሮ የሚያስፈልጋቸው ነገር የሌላቸውን እንረዳለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባለ ዐደራነት ባለ ዐደራው ለሌሎች እንዲሰጥ ብቻ ሳይሆን ለጋስ ሕይወት እንዲኖር ነጻ ያወጣል። ጆን ዌስሊይ የገቢውን 90% በመስጠት በ10% ብቻ ይኖር ነበር። አብዛኛዎቻችን 10% ወይም ከዚያ ያነሰ ሰጥተን ቀሪውን ለራሳችን እንጠቀማለን። እግዚአብሔር ገንዘባችን ያስፈልገዋል? በሺህ ተራሮች ያሉ ከብቶች የእርሱ ናቸው፤ በጫካ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ እንስሳ የእርሱ ነው። እግዚአብሔር ገንዘባችን አያስፈልገውም፤ ነገር ግን ከገንዘብ ፍቅር እንድንላቀቅ እና በእርሱ ላይ በፍጹም እንድንታመን መስጠትን ያስተምረናል። ተግባራዊ የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባለ ዐደራነት ከስግብግብነት፣ ከስስት እና ከመጠን በላይ ከማከማቸት ይጠብቀናል።

የእግዚአብሔር ነቢይ የነበረውን ኤልያስን እና የሰራፕታይቱን መበለት ታሪክ ታስታውሳላችሁ (1ኛ ነገ. 17÷7-16)? በምድሪቱ ላይ ለሦስት ዓመታት ያህል ረሃብ ነበር፤ እግዚአብሔር ትመግበው ዘንድ ኤልያስን ወደ ሰራፕታዋ ሴት መራው። ይህቺ ሴት እርሷና ልጇ አንድ ጊዜ ብቻ የሚበሉት ጥቂት ዱቄትና ዘይት ነበራት፤ ነገር ግን መሥዋዕት በመክፈል ያላትን ምግብ ለነቢዩ ኤልያስ መስጠት ችላለች።

የቤተ ሰቧን የመጨረሻ ምግብ ለነቢዩ መስጠት ያቻለችው እንዴት ነው? ምክንያቱም እግዚአብሔር ልቧን አዘጋጅቶ ነበር፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ለእርሷና ለልጇ እንደሚያዘጋጅ አምና ነበር። እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ከማድጋው ዱቄት፣ ከማሰሮውም ዘይት አላለቀም ነበር።

ትልቁ የልግስና እንቅፋት የንብረቶቻችን ሁሉ ባለ ቤት እኛ እንደ ሆንን ማሰባችን ነው። እኛ ባለ ዐደራዎች እንደ ሆንን እና የሁሉ ባለ ቤት እግዚአብሔር እንደ ሆነ ብንገነዘብ ግን ይህ የእግዚአብሔርን ልብና ፈቃድ ወደ መከተል ይመራናል። ይህ በዚህ ዓለም የምንኖርበትን መንገድ እና ያለንን ቁሳዊ ንብረቶች ሁሉ የምንይዝበትን መንገድ ሙሉ በሙሉ ይቀይር ነበር። ያለን የትኛውም ንብረት የእኛ አይደለም የሚለው ሐሳብ ነጻ የሚያወጣ ሐሳብ ነው! ይህ ከብዙ ጭንቀትና ድባቴ የሚያድን ነው። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ማዘጋጀት ይችላል። ሰዎች በነጻ የሚሰጡበትን እና ለሌሎች የሚያካፍሉበትን ዓለም አስቡ። አንድ የማውቀው ክርስቲያን ባለ ሥልጣን ጥሩ የባለ ዐደራነት ምሳሌ ነው። ይህ ሰው ለክርስቲያናዊ አገልግሎቶች እና ርዳታውን ፈልገው ወደ እርሱ ለሚመጡት ሁሉ ድጋፍ ያደርጋል። ይህ ሰው እንዲህም ይላል፤ "እኔ የእግዚአብሔር ቼክ ፈራሚ ብቻ ነኝ።"

**ሙግት ለቀን አንድ**

ለጋስ ለሆነው እግዚአብሔር የምንሰጠው ምላሽ ለምድራዊ ነገሮች ያለንን ፍቅር ዛሬ በማስወገድ የምንጠይቀውን እና የሚያስፈልገንን አትረፍርፎ በሚሰጠን በእርሱ መታመን በመጀመር ነው። እንደ ባለ ቤት እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን የሚያዘጋጅም ነው። የእኛ ኀላፊነት የእርሱን ፈቃድ በታማኝነት መታዘዝ እና የእርሱን ፍላጎቶች መፈጸም ነው። ይህም አስቀድመን ጽድቁን እና መንግሥቱን መፈለግ ሲሆን ያኔ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ይጨመሩልናል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎቹን እንደሚፈጽም በማመን የእምነት ጉዞ መጀመርን ይጠይቃል፤ ይህን ለመጀመር ደግሞ ጊዜው አሁን ነው። በየዕለቱ ጸጋውን እና መግቦቱን ስንለማመድ እምነታችን እያደገ ይሄዳል።
እነሆ ሙግታችሁ፦

- 1ኛ ጢሞቴዎስ 6÷6-10 እና ማቴዎስ 6÷24 ን አንብቡ።
- ከእርሱ ውጪ ለየትኛውም ነገር ያላችሁን ፍቅር እንዲያስወግድ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ።
- በፍጹም ልባችሁ እግዚአብሔርን መውደድ ትችሉ ዘንድ እርሱ እንዲያስወግድላችሁ የምትፈልጉትን ነገሮች በዝርዝር ጻፉ። ዝርዝራችሁን በፊቱ አስቀምጡ፤ ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ መልሳችሁ ለእርሱ ስትሰጡ ሰንሰለቶች ሁሉ እንደ ወደቁ ይሰማችሁ።

መሥዋዕትነት የተሞላ ሥጦታ እንድትሰጡ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ያነሳሳበትን የመጨረሻውን ጊዜ አስታውሱ። ምን ዓይነት ምላሽ ሰጣችሁ? መንፈስ ቅዱስ ዛሬም እንደ ገና እንዲያነሳሳችሁ ጸልዩ፤ ለሚያነሳሳችሁ ጉዳይ ምላሽ ለመስጠትም ዝግጁ ሁኑ። እግዚአብሔር የሚሰማው ልብ እና ፈቃደኛ መንፈስ እንዲሰጣችሁ ጸልዩ። ያ በሚፈጸምበት ጊዜ በታዛዥነት ምላሽ መስጠት አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ያወጣነውን ሁሉ መተካት (የጎደለውን ሁሉ አትረፍርፎ መሙላት) እንደሚችል እመኑ። ታዘዙ፤ ከዚያም በልግስና በመስጠት እግዚአብሔርን በመታመናችሁ ምን ዓይነት ስሜት እንደ ተሰማችሁ ጻፉ።

የመበለቲቱን ማድጋ በዱቄት፣ ማሰሮውን በዘይት የሞላ የኤልያስ አምላክ ዛሬ እኛ ከምናገለግለው እግዚአብሔር ጋር አንድ ነው።

ከምድራዊ ነገሮች ሁሉ ፍቅር እንዲያላቅቀኝ እና ነጻ እንዲያወጣኝ ዛሬ እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ።

# ቀን ሁለት

## አብርሃም፤ የለጋስ ሕይወት ምሳሌ

BY RICHARD SAMUEL (INDIA)

---

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍል ምንባብ**

"እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ። አብራምም እግዚአብሔር እንደ ነገረው ሄደ ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ አብራምም ከካራን በወጣ ጊዜ የሰባ አምስት ዓመት ሰው ነበረ።" ዘፍጥረት 12÷-4

**ትምህርት**

ስለ ልግስና እና ለጋስ ስለ መሆን ስንነጋገር ከእግዚአብሔር ቃል በልግስና ስለ ተሞላ ሕይወት እንድናጠና እፈልጋለሁ። የአብርሃም ጉዞ በመስጠት የተሞላ የሕይወት ዘይቤን ያሳያል። አንድ ሰው ያለ እግዚአብሔር እርዳታ በልግስና የተሞላ ሕይወት መኖር አይችልም፤ ይህ እናንተ የምታከናውኑት ተግባር ሳይሆን የማንነታችሁ አካል ነው። ለመስጠት እጆቻችንን መዘርጋት የምንጀምረው ከእግዚአብሔር ጋር በጥልቅ ግንኙነት ስንጓዝ ነው። ከእግዘአብሔር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ኖሮን እንድንጓዝ ብቻ ሳይሆን ልግስና ራሱ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ጥልቅ ግንኙነት መሆኑን የሚያስታውሱ ሦስት ነጥቦችን ከአብርሃም ሕይወት እንመለከታለን።
በመጀመሪያ እግዚአብሔር አብርሃም ከአገሩና ከዘመዶቹ ተለይቶ ወደማያውቀው እና እርሱን ወደሚባረክበት ምድር ጠራው። አብርሃምም በመታዘዝ ከካራን ወደ ከነዓን ተጓዘ፤ በዚያም ሥፍራ እግዚአብሔር እንደ ገና ተገልጦለት የቆመባትን ምድር ለእርሱና ለዘሩ እንደሚሰጥ ተናገረው። በምእራፍ 13 በአብርሃምና በሎጥ እረኞች መካከል ግጭት ተፈጠረ፤ ሎጥ የወደደውን ሥፍራ መርጦ እንዲወስድ ዕድል ከሰጠው በኋላ አብርሃም የቀረውን ሥፍራ ወስዶ ከሎጥ ተለየ።

የምድሪቱን ልምላሜ መለስ ብለን ማሰብ ይኖርብናል። ይህ የተስፋ ቃል የተሰጠው ሰው የተስፋይቱን ምድር ለሎጥ አሳልፎ ሰጠ። በዚያ ምሽት በድንኳን ውስጥ አብርሃም ከሣራና ከእረኞቹ ጋር ምን ዓይነት ንግግር አድርጎ እንደሚሆን በኅሊናችሁ አስቡ፤ ምናልባትም እነዚህ ሰዎች የተሸነፉ ወይም በእጃቸው ያለውን ነገር አሳልፈው እንደ ሰጡ እና እንዳጡ ተሰምቷቸው ይሆናል።

ወደ ሎጥና እረኞቹ ድንኳን ደግሞ ገብታችሁ አስቡ፤ በዚያ ምሽት ምን ዓይነት ንግግር አድርገው ይሆን? ምናልባትም አብርሃምን በብልጠት እንደ በለጡት እና በሁሉ ነገር እነርሱ እንዳሸነፉ ተሰምቷቸው ይሆናል። በዚያ ምሽት በአብርሃም አእምሮ ምን ተመላልሶ ሊሆን እንደሚችል አስቡ፤ ምናልባትም ባደረገው ነገር የተለያዩ ጥያቄዎች ተፈጥሮውበት እና ጥርጣሬ ውስጥ ገብቶ ሊሆን ይችላል። ሎጥ ለምለም የሆነውን እና ለከብቶች በጣም ተፈላጊ የሆነውን መልካም ሥፍራ መረጠ፤ የቀረው ጠንካራና ድንጋያማ የሆነ አከባቢ ለአብርሃም ቀረ።

ይህ ሁሉ የአብርሃም ምርጫ ነበር፤ ወዲያውኑ ዓይኖቹ ስብር ብለው ተስፋ መቁረጥ በፊቱ ላይ ይነበብ ነበር። ታላቅ ለጋስነቱን ባሳየበት ወቅት በጣም ደካማ ሆኖ ታየ፤ በጥርጣሬ እና

ምናልባትም በፍርሃት ውስጥ ወድቀ፤ እግዚአብሔር ግን ይህን ሁሉ ያውቅ ነበር። ሁሉን የተመለከተው/የሚያውቀው እግዚአብሔር ወደ እርሱ መጣ፤ እንዲህም ያለው ይመስላል፤ “ጥሩ አድርገሃል አብርሃም!”

“ሎጥ ከተለየው በኋላም እግዚአብሔር አብራምን አለው። ዓይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ስፍራ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ እይ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጣለሁና። ዘርህንም እንደ ምድር አሸዋ አደርጋለሁ የምድርን አሸዋን ይቈጥር ዘንድ የሚችል ሰው ቢኖር ዘርህ ደግሞ ይቈጠራል። ተነሣ በምድር በርዝመትዋም በስፋትዋም ሂድ እርስዋን ለአንተ እሰጣለሁና።” (ዘፍጥረት 13÷14-17)

ሎጥ ተለይቶት ከሄደ በኋላ ወዲያውኑ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ ለለጋስነቱ ምላሽ ሰጠ፤ እንዲህም አለ፤ “አንተን ማእከል/ዋና አደርግሃለሁ፤ በአራቱም አቅጣጫ ባለህበት ሥፍራ ዙርያ ያሉት ሁሉ ያንተ ናቸው! የምትመለከታቸሁ ሁሉ ያንተ ናቸው!” ከዚያም እንዲህ አለው፤ “ተነሣ በምድር በርዝመትዋም በስፋትዋም ሂድ እርስዋን ለአንተ እሰጣለሁና።” አብርሃምና እግዚብሔር ያላቸውን ነገር እየተሰጣጡ ያለ ይመስላል!

ሁለተኛው ክስተት የሚገኘው በዘፍጥረት ምእራፍ 14 ላይ ነው። አራት ነገሥታት ሳብረት ፈጥረው የሰዶምን ንጉስ ድል አደረጉ፤ ሎጥና ቤተ ሰቡ እንዲሁም ንብረቱ ሁሉ በእነዚህ ነገሥታት ተወሰዱ። አብርሃም ይህንን ሲሰማ የራሱን ሰዎች ይዞ አራቱን ነገሥታትና ሠራዊቶቻቸውን በማሳደድ ከደማስቆ ባሻገር ላይ ድል አደረጋቸው። እረኞቹ ከብቶቹን የሚያሰማሩበትን ሥፍራ የተወው አብርሃም ሎጥንና ቤተ ሰቡን ከነንብረቶቻቸው አስመለሰ።

የሰዶም ንጉሥ ያስመለሰውን ሕዝብ እንዲሰጠው እና ሐብቱን/ንብረቱን ሁሉ ግን ለራሱ እንዲወስድ ለአብርሃም ግብዣ አቀረበ። አብርሃም ግን “አይሆንም፤ ሁሉንም ለራስህ አድርገው” በማለት ምላሽ ሰጠ። አብርሃም የወጣው ትርፍ ወይም ለራሱ ጥቅም ለማግኘት አልነበረም። እርሱ መበልጸግ ካለበት ብልጽግናው የሚመጣው ከጌታ ከእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ብቻ ነበር። ሌላውን ሁሉ አይቀበልም። ይህ ምን ዓይነት ከፍ ያለ መንገድ (አካሄድ) ነው? ለእርሱ የሚያስፈልገውን የሚያዘጋጀው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ወደ ቤቱ እየተመለሰ በነበረበት ጊዜ በውስጡ ምን ይሰማው እንደ ነበረ በምናባችሁ አስቡ። አራት ነገሥታትን እና ሠራዊቶቻቸውን ድል አድርጓል፤ የሰዶም ንጉሥንም አስቆጥቷል። ቢያንስ አምስት ነገሥታትን ጠላቶቹ እንዲሆኑ አድርጓል! ሆኖም አብርሃም ከመፍራቱ በፊት እግዚአብሔር ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ በግልጽ ቋንቋ ተናገረው፤ እንዲህም አለው፤ “አብራም ሆይ፦ አትፍራ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው” (ዘፍጥረት 15÷1)። እግዚአብሔር ለአብርሃም እያለ የነበረው፣ “ይህንን በማድረግህ አትጸጸት። እኔን መታዘዝህን ቀጥል የቀረውን ሁሉ እኔ እቆጣጠረዋለሁ። በከፍታ መጓዙን ቀጥል፤ አንሰህ ራስህን አታሳንስ! ይህንን ማድረግ ትችላለህ። እኔ ስለምጠብቅህ ምንም አያገኝህም።“ ከዚያ በኋላ አስቀድሞ ከተሰጠው ተስፋ በላይ እግዚአብሔር ሠፊ ርስት ወይም ግዛት እንደሚሰጠው መግለጹን እንመለከታለን። ከግብጽ ወንዝ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ያለው ምድር ሁሉ የእርሱ እንደሚሆን ተነገረ። አስቀድሞ ከነዓን አሁን ግን በከነዓን ዙርያ ያሉት አከባቢዎች ሁሉ የእርሱ እንደሚሆኑ ተገለጸ።

በመጨረሻም የተስፋው ልጅ ከተወለደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አብርሃም አንድ ልጁን ይስሐቅን በሞሪያም ተራራ እንዲሰዋለት እግዚአብሔር ጠየቀው። አብርሃም ይህንንም ጥያቄ ወዲያውኑ በመቀበል እግዚአብሔርን ሲታዘዝ እናያለን። በዘፍጥረት 22÷3 መሠረት “አብርሃም በማለዳ ተነሣ።” ምንም ዓይነት ጥያቄዎች አላነሳም፤ የእርሱን ፈቃደኝነት በተመለከተ ወይም ይስሐቅ ብቸኛው የተስፋ ልጁ መሆኑን በተመለከተ ምንም ዓይነት ሙግት አልገጠመም። አብርሃም የተለየ ሰው ነው። እግዚአብሔር ከተናገረ አብርሃም በመታዘዝ ለመፈጸም ይነሳል። በዚህም ታሪክ አብርሃም የማይታመን ነገር ለማድረግ በተነሳ ጊዜ እግዚአብሔር የመሥዋዕቱን በግ በማዘጋጀት ጣልቃ ገባ። አብርሃም ያለውን ሁሉ የሰጠ፣ በሕይወቱ ውስጥ እጅግ በጣም ውድ ለነበረው ለልጁ እንኳን ያልራራ ሰው ነው። እግዚአብሔር የሚያድን እና በመባረክ ወሮታን የሚመልስ አምላክ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ማንንም ባርኮ በማያውቅበት መንገድና በረከት የአብርሃምን ትውልዶች ባረከ። እግዚአብሔር ለአብርሃም “አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና” በማለት ለታማኝነቱ ዕውቅና ሰጠ። የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ በዚሁ በሞሪያም ተራራ ላይ መሰጠቱ የአጋጣሚ ጉዳይ አይመስልም።

**ሙግት ለቀን ሁለት**

ከእነዚህ ከሦስቱ ትምህርቶች እኛ የምንማረው፤ (1) አብርሃም አስቀድሞ ሎጥ የፈለገውን መሬት መርጦ እንዲወስድ በማድረግ ለእርሱ የቀረውን ሥፍራ እግዚአብሔር በፈለገው መንገድ እንደሚባርክለት እንዳመነ ሁሉ እኛም ያለንን (የእኛ ነው ብለን የምናስበውን) ሁሉ በመስጠት እርሱ እንደሚያዘጋጅልን እንድናምን እግዚአብሔር ይጠይቀናል፤ (2) የሚያስፈልገንን ሁሉ የሚያዘጋጅልን ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ እናም የእርሱን ሥፍራ እንዲተካ ወደ ማንም ልንመለከት አይገባም፤ (3) እግዚአብሔር እንድንሰጥ የሚጠይቀን ነገር የቱንም ያህል ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም ለጋስነት ምን ጊዜም ቢሆን ደስታና ከእግዚአብሔር ዘንድ የተትተፈረፈ መግቦት ማስከተሉ አይቀርም።

እነሆ ሙግታቸሁ፦-

- 2ኛ ቆሮንቶስ 8÷1-7 ን አንብቡ።
- ከምንም ነገር በላይ እግዚአብሔር በእርሱ የሚታመን ልብ እንዲሰጣችሁ ጸልዩ።
- በሚያስገርምና በሚያስደንቅ መልኩ እግዚአብሔር ለጥያቄዎቻችሁ መልስ የሰጠባቸውን ጊዜያት አስታውሱ። እነዚህን ያስታወሳችሁትን የእግዚአብሔርን ታማኝነት የሚያሳዩ መግቦቶች በዝርዝር በመጻፍ ለአንድ ሰው መስክሩ።

ማድረግ ፈልጋችሁ ያቃታችሁን እና አሁን እግዚአብሔር እንደሚያዘጋጅ በማመን ማድረግ የምትፈልጉትን አንድ ነገር ጥቀሱ፤ ለጋስነታችሁን እንደ ሞኝነት/አለማወቅ ቆጥረው በእናንተ መጠቀም የሚፈልጉ ቢኖሩ እንኳን ማለት ነው። ይህንን ጉዳይ ለእግዚአብሔር መልሳችሁ ስጡና በእርሱ ዕረፉ። ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚያስፈልጋችሁን እንደሚያዘጋጅላችሁ የተማመናችሁበትን የአንድ ሰው ስም ጥቀሱ። መታመን የሌለባችሁን ስለ ታመናችሁ ንስሐ ግቡ፤ ልክ እንደ አብርሃም በእርሱ ብቻ መታመን እንድትችሉ እግዚአብሔር ኀይል እና ብርታት እንዲሰጣችሁ ጸልዩ። ለጋስ ሕይወት እንዲኖራችሁ ለቀረበላችሁ ጥሪ ታዛዥ መሆናችሁን ለማሳየት እግዚአብሔር ዛሬ እንድትሰጡ የሚጠይቃችሁ አንድ ነገር ካለ ጥቀሱ። ታዛዥ ለመሆን፣ እርሱ የጠየቃችሁን ያንን ነገር ለመስጠት እና የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ እርሱ ራሱ ሲያዘጋጅላችሁ ለማየት ዛሬ ወስኑ።

እኔ የተቆጣጠርኳቸውን እና የእኔ የምላቸውን ነገሮች ለቅቄ የሚያስፈልገኝን ሁሉ የሚያዘጋጅልኝ እርሱ እንደ ሆነ መታመን እንድችል እግዚአብሔር እንዲረዳኝ እጸልያለሁ።

# ቀን ሦስት

## የገንዘብ (የፋይናንስ) ባለ ዐደራነት፤ ያለንን ሁሉ መስጠት

BY MIKE O'NEILL (UNITED KINGDOM)

---

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍለ ምንባብ**

«እውነት እላችኋለሁ፣ ይህች ድሀ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች፤ እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና፤ ይህች ግን ከጕድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አለ።» (ሉቃስ 21÷3-4)

**ትምህርት**

የአንተ "ሁሉ" ምን ይመስላል?
በእነዚህ አጭር ቁጥሮች ገንዘባችንን በደስታ ማስተዳደርን በተመለከተ ከሚያስተምሩ እና መሠረታዊ ከሆኑ ምሳሌዎች መካከል አንዱን እናገኛለን፤ ይህ ትምህርት የቀረበው ደግሞ በመበለቷ ታሪክ ነው። መበለቶች (እና ሚስት የሞቱባቸው ሰዎች) ሁል ጊዜ የሚኖሩት በጕድለት ነው። ከጕድለታቸው፣ ከስቃያቸው እና ከልባቸው ጭንቀት በተጨማሪ ሁል ጊዜ የባሎቻቸው ወይም የሚስቶቻቸው አለመኖር የፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ይታገላሉ፤ ይህ ደግሞ አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ እና ተግባራዊ (የገንዘብ) ተጽእኖ አለው። በአንደኛው ክፍለ ዘመን ለምትኖር መበለት ሕይወት በከፍተኛ ትግል የተሞላ ነው።

በሉቃስ 20 ኢየሱስ የምድር ሕይወቱ የመጨረሻ ጊዜያት አከባቢ ላይ እንደ ደረሰ እንመለከታለን፤ በዚህ ወቅትም በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የተለያዩ ቡድኖችን ያስተምር ነበር፤ ከእነዚህም መካከል ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን፣ የሕግ መምህራን እና ደቀ መዛሙርቱ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ማስተማር ኢየሱስ ቅድምያ የሚሰጠው ጉዳይ ነበር።

ቀና ብሎ ሲመለከት ግን ከሁሉ ይበልጥ ጠቃሚ የሆነ አንድ ክስተት ትኩረቱን ሳበ። አንዲት ስሟ ያልተጠቀሰ መበለት ወደ ፊት ወጥታ በእግዚአብሔር በመታመን ያላትን ሁሉ ስትሰጥ ተመለከተ (ምናልባትም ሌሎች ያዩአት አይመስልም)። ይህቺ መበለት ያላትን ሁለት ሳንቲም ሰጠች።

ለጥቂት ደቂቃ ቆም ብለን ይህቺ ሴት የፈጸመችውን ይህን አንድ ተግባር እና ይህ ተግባሯ ገንዘባችንን እንደ ባለ ዐደራ እንዴት መያዝ እንዳለብን ምን እንደሚያስተምረን እንመልከት። የቤተ መቅደሱ ግምጃ ቤት እና የገንዘብ ቤት የተዘጋጀው በሁለት ቡድኖች ውስጥ ለሚገኙ ወገኞች ነው፤ እነርሱም፣ ሌዋውያን የነበሩ ካህናት (ምንም ዓይነት ንብረት የሌላቸውና የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ነገር በቤተ መቅደስ ከሚሰበሰበው የሚያገኙ) እና ድኾች፣ መበለቶችና ወላጅ አልባ ልጆች ናቸው። የገንዘብ ድጋፍ እና ማኅበራዊ ደኅንነት የሚያገኙበት መንገድ ነው።  ከቤተ መቅደሱ ግምጃ ቤት የሚያስፈልጋቸውን የሚቀበሉ ሰዎች ሁሉ የገቢ ምንጫቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ በደስታ የሚለግሰው ስጦታ ነው። ብዙ ያላቸው ይሰጣሉ፤ ምንም የሌላቸው ደግሞ ይቀበላሉ።

በድንገት ግን ይህቺ መበለት የተለመደውን ሥርዓት ገልብጣ በአፍ ጥሙ ደፋችው። በሥርዓቱ መሠረት ለሚያስፈልጋት ከገንዘብ ቤቱ የመውሰድ መብት ነበራት። እርሷ ግን ከመቀበል ይልቅ ሰጠች! (መቀበል ሲገባት/እየቻለች ሰጠች)።

ይህንን ከኢየሱስ ውጪ ማንም አላስተዋለም። ቆም ብሎ በመገረም አየ፤ ይህቺ መበለት በፈጸመችው ተግባር ልቡ ተነካ፤ ያላትን ሁሉ እንደ ሰጠች ተናገረ። የነበራትን ትዳርዋን "ሁሉ" በሚለው ላይ ትኩረት አደረገ፤ ሁሉ የሚለውን ሐሳብ በሁለት ዐረፍተ ነገር ውስጥ ወደ ሦስት ጊዜ በመደጋገም ለደቀ መዛሙርቱ ተናገረ። ያላትን ሁሉ ሰጠች፤ ያስቀረችው አንዳች ነገር የለም።

በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረችው መበለት ታሪክ ምሳሌ (PARABLE) ወይም ድኾች እንኳን እንዴት እንደሚሰጡ ለማስተማር የተፈበረከ ጥሩ ታሪክ አለመሆኑን ልብ በሉ። ይህ በትክክል የተፈጸመ ታሪክ ነው። በዚህ የሆነ ጊዜ በአንድ ሥፍራ በትክክል በተፈጸመ ክስተት ኢየሱስ እያከናወነ የነበረውን ተግባር አቋረጠ፤ ምክንያቱም እውነተኛነትን ተመልክቷልና።

የእርሷን ሥጦታ ትኩረት ሰጥቶ በማብራራት ሊሆን ያለውን የራሱን ስጦታነት አስቀድሞ አመላከተ፤ ዕብራውያን 12÷2፣ "እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።" እኛም ይህንን ደስታ ማግኘት/መለማመድ የምንችለው በመስጠት ውስጥ ነው፤ ይህ ደስታ ደግሞ በምንሰጥበት ቅጽበት ብቻ የሚከሰት ሳይሆን ዘላለማዊ ነው።

ዊሊያም ቦርደን በሉቃስ እንደ ተጠቀሰችው ደኻ መበለት ትክክለኛ ሰው ነው። ይህ ሰው ግን እጅግ ባለ ጸጋ ነበር። የሀብቱ ምንጭ ባለፈው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አከባቢ ላይ ከትልቅ ቤተ ሰቡ የወረሰው ውርስ ነበር፤ ይህ ወጣት ሰው ምንም ሳይደክምና ሳይጠይቅ በአንድ ጊዜ ዓለም በእጆቹ መዳፍ ላይ የሆነች ያህል ተሰማው። በ1904 ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመረቀ በኋላ ወደ ዩኒቨርሲቲይ ከመግባቱ በፊት ወደ ተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ለመጓዝ ወሰነ። በጉዞው የተመለከታቸው የተጎዱ ሰዎች ግን ዕቅዱን ቀይረው ሚስዮናዊ ለመሆን ተነሣሣ። በመጽሐፍ ቅዱሱ ጀርባ ላይ ሁለት ቃላትን ጻፈ፤ "በፍጹም አልቆጠብም።"

ቦርደን ከየል ዩኒቨርሲቲይ ከተመረቀ በኋላ የቀረቡለትን የሥራ አማራጮች ሁሉ አልተቀበለም። በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ሁለት ተጨማሪ ቃላትን ጻፈ፤ "በፍጹም አላፈገፍግም።" ትምህርቱን በሴሜናሪይ ቀጥሎ ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ቻይና ለመጓዝ ተነሣ። ሙስሊሞችን ለመድረስ በማሰብ በግብጽ ጥቂት ቆይቶ የአረብኛ ቋንቋ ተማረ። በዚያም ሥፍራ ማጅራት ገትር ይዞት በመታመሙ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሃያ አምስት ዓመቱ ወጣት ሞተ።

ዊልያም ከመሞቱ በፊት ሁለት ተጨማሪ ቃላቶችን በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ጽፎ ነበር። "በፍጹም አልቆጠብም" እና "በፍጹም አላፈገፍግም" ከሚሉት ጽሑፎች ሥር "በፍጹም አልጸጸትም" የሚለውን ጨምሮ ጻፈ።

ብዙ ጊዜ የመበለት ወይም ሚስት የሞተበት ሰው ትልቁ ፍላጎት በእጅ ያለውን አነስተኛ ነገር መቆጠብ እና አጥብቆ መያዝ ነው። ብዙ ሀብት ያለው ሰው እርዳታ የሚያስፈልገው ችግር ሲመለከት የመጀመሪያው ምላሽ ቼክ መጻፍ፣ አንድ ሌላ ሰው መላክ፣ ወይም የሚያስፈልገውን /የሚበቃውን "ጥቂት ነገር" ማድረግ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ዊልያም ቦርደን እና ስሟ ያልተጠቀሰው መበለት የሰጡት ያላቸውን ሁሉ ነበር። ይህም ነው እነዚህን ሰዎች ከኢየሱስ ጋር የሚያመሳስላቸው።

ስሟ ያልተጠቀሰው መበለት ምን ዓይነት ሕይወት ሊኖረን እንደሚገባ እና በምን መልኩ መስጠት እንዳለብን ታስተምረናለች። ዊልያም ቦርደን ደግሞ ቁሳዊ ብልጽግናም ሆነ ድኅነት ምንም አለመሆናቸውን ያሳየናል።

**ሙግት ለቀን ሦስት**

እና ምን ይሁን? ይህ ገንዘባችንን ከመስጠት ጋር ይገናኛል? ያለን ጥቂትም ይሁን ብዙ በደስታ የመስጠት መሠረት ያለን "ሁሉ" ምን እንደሚመስል ከመረዳት ይመጣል።

**እነሆ ሙግታችሁ፡-**

- ሉቃስ 12÷15-20 እና ማቴዎስ 13÷44 ን አንብቡ።
- የእናንተን "ሁሉ" በሚገባ መግለጽ እንድትችሉ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጸልዩ። በዝርዝር በመጻፍ በእግዚአብሔር ፊት አስቀምጡት። በጣም ለሚቀርባችሁ ሰው አካፍሉ። ከእናንተ ጋር ይስማማሉ?
- ምንም ዓይነት ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያዘጋጅ በማመን ጠንክራችሁ መቆም እና ያላችሁን "ሁሉ" መልሳችሁ ለእግዚአብሔር ለመስጠት ራሳችሁን በመስጠት ምላሽ ስጡ።

መበለቷ እና ወራሹ ያላቸው ሁሉ ምን እንደ ሆነ አውቀዋል። ሁለቱም መስጠትን ቀለል አድርገው የወሰዱ፣ ለመስጠት ዝግጁ የሆኑ እና ያላቸውን ሁሉ ለመስጠት ፈቃደኞች የሆኑ ነበሩ፤ ይህንንም በማድረግ ከምድራዊ ደስታ የላቀውን ዘላለማዊ ደስታ መፈለጋቸውን አሳይተዋል። ዘላለማዊው ደስታ ያለንን ሁሉ የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፤ "በፍጹም አንቆጠብም" እንዲሁም "በፍጹም አንጸጸትም።"

የእኔ ናቸው የምላቸውን "ሁሉ" በትክክል መዘርዘር እንድችል እና በሕይወቴ ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ አንዳች ነገር እንዳላስቀር እንዲረዳኝ ዛሬ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ።

# ቀን አራት

## ለጋስ ሕይወት፤ ተነሳሽነትን ቀድሞ መውሰድ

BY KEHINDE OJO (NIGERIA)

---

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍለ ምንባብ**

"አንድ ቀንም እንዲህ ሆነ ኤልሳዕ ወደ ሱነም አለፈ፥ በዚያም ታላቅ ሴት ነበረች እንጀራ ይበላ ዘንድ የግድ አለችው በዚያም ባለፈ ቍጥር እንጀራ ሊበላ ወደዚያ ይገባ ነበር። ለባልዋም። ይህ በእኛ ዘንድ ሁልጊዜ የሚያልፈው ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ሆነ አውቃለሁ። ትንሽ ቤት በሰገነቱ ላይ እንሥራ በዚያም አልጋ ጠረጴዛ ወንበርና መቅረዝ እናኑርለት ወደ እኛም ሲመጣ ወደዚያ ይገባል አለችው።" (2ኛ ነገሥት 4÷8-10)

**ትምህርት**

ነቢዩ ኤልሳዕ ከነበረው አገልግሎት የተነሣ ሰዎች ወደ እርሱ የሚመጡበት ቀዳሚው ምክንያት ከእርሱ አንድ ነገር ፈልገው ቢሆን ይህ ያልተለመደ አይደለም። ምናልባት እርሱ ብዙ ያልለመደው ነገር ቢኖር ከእርሱ ምንም ምላሽ ሳይጠብቁ ለእርሱ መልካምነት እና ለጋስነት የሚያሳዩ ሰዎችን ነው። ኤልሳዕ ወደ ሱነም በወረደ ጊዜ በትክክል የተከሰተው ይህ ነበር። አንዲት ባለጸጋ ሴት ወደ ቤቷ ስትጋብዘው ምናልባትም ኤልሳዕ ያሰበው ገንዘብ ሊፈታ ያልቻለው አንዳች ዓይነት ችግር በቤተ ሰቧ ውስጥ መኖሩን ይሆናል። ይህ ቤተ ሰብ ነጻ መውጣት፣ ከሕክምና በላይ የሆነ ሕመም ፈውስ ያስፈልጋቸው ይሆናል ብሎ አስቦ ይሆናል። በትክክልም አንዳች ዓይነት መንፈሳዊ ጣልቃ ገብነት እንደሚያስፈልጋቸው አስቧል።

ይህ ቤተ ሰብ ከእግዚአብሔር ሰው አንዳች ዓይነት እርዳታ ከመጠየቅ ይልቅ ተነሳሽነቱን ወስደው እጅግ በጣም አድካሚ ከነበረው ጉዞ በኋላ ካላቸው ነገር ላይ ይመገብ ዘንድ ግብዣ አቀረቡለት። ይህች ባለ ጸጋ ሴት ኤልሳዕ እንዲበላ የግድ ማለቷ እንግዶችን (ወይም የማይታወቁ የሌላ አገር ሰዎችን/መጻተኞችን) ወደ ቤታቸው በመጋበዝ ምግብ እንዲበሉ ማድረግ ለእርሷ ቤተ ሰብ የተለመደ ተግባር መሆኑን ያሳያል (2ኛ ነገሥት 4÷8)። አስደናቂ ነው! ምግብዋን ለመስጠት ዝግጁ ናት፤ በምላሹ ከእርሱ አንዳች ነገር ለማግኘት ወይም ለመቀበል ግን አልነበረም። ምን ዓይነት የለጋስነት መንፈስ ነው! ገበታው የተትረፈረፈ እና ግብዣውም ከልብ በመሆኑ ኤልሳዕ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከዚህ ቤተ ሰብ ጋር ተቀራረበ፤ የዘውትር ተመላላሽ እንግዳም ሆነ። ይህች ሴት ከባሏ ጋር በመመካከር ትንሽ ቤት በሰገነት ላይ ለኤልሳዕ ለመሥራት በመወሰን የልግስናቸውን መጠን እጅግ ከፍ አደረገችው። ለዚህ ከቦታ ቦታ ለሚዘዋወር አገልጋይ ገንዘባቸውን አውጥተው ትንሽ ቤት በሰገነት ላይ ለመሥራት ፈቃደኞች ሆኑ። እነዚህ ሰዎች የሚያስፈልገውን ቤትና የቤት ቁሶች ሁሉ በማዘጋጀት እንግዳቸው ተመችቶት በእነርሱ ዘንድ እንዲያርፍ ያደረጉትን ልብ በሉ (ቁ. 10)።

ዛሬም ቢሆን ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚሰጡ መጥቀስ አስፈላጊ ነው፤ ይሁን እንጂ ሁሉም ስጦታዎች በንጽሕ ልብና በቅንነት የሚደረጉ ናቸው ለማለት ይገብዳል። ኤልሳዕ ይህ ቤተ ሰብ ከአሁን አሁን አንድ ጥያቄ ያቀርባል ብሎ አስቦ ይሆናል፤ ነገር ግን እስኪደነቅ ድረስ የቤተ ሰቡ ፍላጎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማገልገል ወደ እነርሱ ቤት ለሚመጡት ሁሉ በረከት መሆን ብቻ ነበር። ኤልሳዕ እንዲህ ዓይነት በጎነት/መልካምነት በምን ምክንያት እንዳሳዩት ለማወቅ ፈልጎ አጥብቆ በጠየቀ ጊዜ የሴትዮዋ ምላሽ እርሷና ቤተ ሰቧ በሰላምና ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ መሆኑን ገለጸች። ለጋስነታቸው የመነጨው ከነጻ ፈቃድ እና ለማገልገል ከመፈለግ

ብቻ ነበር። ይህ በመስጠት ያለውን ደስታ የሚለማመዱበት ምን ዓይነት አስገራሚ ነጻነት ነው!

እነዚህ ሰዎች ግለ ሰቦች፣ ቤተ ሰቦች ወይም ተቋማት መስጠት ያለባቸው አንዳች ዓይነት እሴት ለመጨመር እንጂ በሰጡት ምትክ በሚያገኙት ነገር ላይ አተኩረው መሆን እንደሌለበት ይሞግቱናል።

ይህ ልዩ ታሪክ በልግስና መስጠትን በተመለከተ አንድ ሌላ ቁልፍ መርሆ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። እነዚህ ባልና ሚስት የሰጡት ስለ ተጠየቁ ሳይሆን በራሳቸው ተነሳሽነት ነው። ልዩነት ለመፍጠር ሁል ጊዜ አጋጣሚዎችን የሚጠባበቁ ወይም የሚፈልጉ ይመስላሉ። በምንም ሁኔታዎች ወይም ባሕል ሳይገደብ ይህን መልካም ጠባይ ሁሉም ሊፈልገው ይገባል።

**ሙግት ለቀን አራት**

ልግስና የልብ መሰጠትን እና እጆች በመዘርጋት መሳተፍን ይጠይቃል። የምናምናቸውን ነገሮች በተግባር እንድንፈጽማቸው ተጠርተናል። በኤልሳዕ ታሪክ አንድ ቤተ ሰብ ተነሳሽነቱን በመውሰድ ለጋስነታቸን በሚታይ መንገድ በተግባር ገለጹ። እኛም ተመሳሳይ ተግባር እንድንፈጽም ተጠርተናል፤ ዕድሉም ተሰጥቶናል።

**እነሆ ሙግታችሁ፡-**

- 1ኛ ጢሞቴዎስ 6÷17-19 ን አንብቡ።
- መሥዋዕትነት የሚጠይቅ ስጦታ በመስጠት ደስታን እንዲሰጣችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ።
- እግዚአብሔር በልባችሁ የሚያስቀምጠውን በመታዘዝ ምላሽ ስጡ። ከሚከተሉት መካከል አንዱን ወይም ሁሉንም በመፈጸም በቋሚነት በመስጠት መሳተፍ እና በልግስና ሕይወት መኖር ትፈልጉ ይሆናል።
  - ለሚስዮን አገልግሎት የሚውል “ፈንድ” ፍጠሩ።
  - ከዚህ ፈንድ ማን እንደሚጠቀም ወስኑ።
  - ጥያቄ ቢቀርብላችሁም ባይቀርብላችሁም ልትረዱ የፈለጋችሁትን አካል በቋሚነት ለመርዳት ቃል ግቡ።
  - ጓደኞቻችሁ፣ ቤተ ሰብ እና በእናንተ ዙርያ ያሉ ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈጽሙ ሞግቱአቸው።

ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ ወይም የእናንተ ቸርነት የሚያስፈልጋቸውን ግለ ሰቦች፣ ቤተ ሰብ፣ የሚስዮን ሥራ የሚሠራ ድርጅት ወይም መልካም ሥራ በጸሎት ምረጡ። ይህ ድጋፍ ችሎታችሁን፣ ጊዜያችሁን ወይም ገንዘባችሁን ሊያካትት ይችላል። ምናልባት ጉብኝት ማድረግ፣ ሥጦታ መግዛት፣ አገልግሎት መስጠት፣ የምክር ወይም የማበረታታት አገልግሎት መስጠት፣ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣ መጸለይ፣ ምግብ ማብላት፣ ወዘተ. ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። በመንፈስ ቅዱስ በመመራት እንዲህ ዓይነት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች፣ ቤተ ሰቦች ወይም ድርጅቶች በመለየት መንፈስ ቅዱስ በልባችሁ ውስጥ ያስቀመጠውን ፈጽሙ።

ዛሬ አንድ ሰው ወይም አገልግሎት በመምረጥ መንፈስ ቅዱስ እንደ መራኝ ጊዜዬን፣ ችሎታዬን ወይም ገንዘቤን መሥዋዕትነት የሚያስከፍል ቢሆን እንኳን እሰጣለሁ።

# ቀን አምስት

## ዝግጁነት፤ ዕቅዳዊ/ሥልታዊ ልግስና

BY GARY WILLIAMS (AUSTRALIA)

---

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍለ ምንባብ**

“እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።” (ኤፌሶን 5÷15-16)

**ትምህርት**

እንዲህ የሚል አንድ ታዋቂ አባባል አለ፤ ይኸውም፣ “ለአንድ ሰው ዓሣ ብትሰጠው አንድ ቀን ይበላል። አንድን ሰው ዓሣ ማጥመድ ብታስተምረው ግን በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይመገባል።” ዓሣ መስጠትም ሆነ ስለ ዓሣ አጠማመድ ማስተማር አንድ ልግስናችንን የሚያሳይ አነስተኛ ተግባር ቢሆንም ውጤታቸው ግን እጅግ ሠፊ ልዩነት አለው። የልማት ድርጅቶች የዚህን ሐሳብ ሥልታዊ ጠቀሜታ ገና ድሮ ተገንዝበዋል። የልግስና መንፈስ ድንቅ ነው፤ ነገር ግን ዕቅዳዊ ወይም ሥልታዊ ሲሆን በትክክል ሕይወት ለዋጭ ይሆናል። ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክት “እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ” በማለት እንዴት መኖር እንዳለብን ይናገራል። ይህ ሐረግ በጥንቃቄ መመልከትን፣ በጥልቀት ማሰብን እና ከተለመደው በላይ ትኩረት ማድረግን ያመለክታል። የምናገኘውን አጋጣሚ ወይም ዕድል በአግባቡ መጠቀም ይህን ሐሳብ ይበልጥ አጉልቶ ያሳያል። ዕድሎችን ለይቶ ማወቅ እና በዕድሎቹ መጠቀም ብቻ ሳይሆን እስከ መጨረሻው ጨምቀን ማድረግ የምንችለውን ሁሉ በማድረግ ዕድሎቹን በአግባቡ መጠቀም ይኖርብናል። አንዳንዶቹን አጋጣሚዎች ወይም ዕድሎች ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን አጋጣሚ ወይም ዕድል በእንዲህ ዓይነት መልኩ መጠቀም ይኖርብናል!

በአገልግሎቴ የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት የምናገለግለውን አገልግሎት ሐሳብ ይደግፋል ብዬ የማስበውን አንድ ተቋም በገንዘብ እንዲረዳን ጠየኩ። 10,000 (አሥር ሺህ) ዶላር ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ እንደምናገኝ ትልቅ ተስፋ ነበረኝ። ከዚህ ተቋም ያገኘሁት ምላሽ፣ “አሁን 10,000.00 (አስር ሺህ) ዶላር እንሰጥሃለን፤ ከሌሎች ምንጮች ተጨማሪ 10,000.00 (አስር ሺህ) ዶላር ማግኘት ከቻልክ ደግሞ እኛም ተጨማሪ 10,000.00 (አስር ሺህ) ዶላር እንሰጥሃለን” የሚል ነበር።

በመጀመሪያ በልግስናቸው እጅግ ተባረኩ። እኛ ራእይ ነበረን፤ እነርሱ ደግሞ ለማገዝ ደስተኞች ነበሩ። እንደውም ከዕቅዳዊ/ሥልታዊ ልግስናቸው የተነሳ ሁለት እጥፍ (በእርግጥ ሦስት እጥፍ) ተባርኬያለሁ። የእነርሱን ምላሽ ይዘን ሌሎችም በተመሳሳይ መልኩ የሚያስፈልጉንን እንዲረዱን መሞገት ችለናል፤ በመጨረሻም 30,000.00 (ሠላሳ ሺህ) ዶላር አገኘን። ግን ምን እንደ ሆነ ገምቱ? የተባረክነው እኛ ብቻ አልነበርንም። የጠየቅነውን ድጋፍ የሰጡትም ተደስተው ነበር፤ ምክንያቱም ስጦታቸው በዕቅድ ወይም ሥልታዊ በሆነ መልኩ በሁለት እጥፍ አድጎ ነበር፤ የመጀመሪያዎቹ ረጂዎቻችንም ተጨማሪ ድጋፍ በማግኘታችን ተበረታተዋል፤ ተደስተዋል። እናም ተልእኮአችን ይበልጥ ሠፋ ወይም አደገ።

ይህ የሥልታዊ ወይም በዕቅድ መስጠት ትንሽ እና የተለመደ ምሳሌ ነው። ወሰብሰብ በሚለው

በሌላኛው የሚዛኑ ጫፍ ያየን እንደ ሆነ ደግሞ ብልጥ እና ለጋስ የሆኑ ሰዎች ልማት፣ ልግስናን እና የሥራ ፈጠራን በማገናኘት አስገራሚ ነገሮች ያደርጋሉ። በተለያዩ መንገዶች የቀረቡላችሁን ዕድሎች ጥቂት ቆም ብላችሁ አስቡ፤ ለምሳሌ፣ ዝቅተኛ የወለድ መጠን ያለው የቤት መግዣ ብድር ወይም በዓለም ዙርያ የሚገኙ ክርስቲያኖች ለጡረታ ከሚያጠራቅሙት ትሪሊዮን ዶላሮች ላይ ሊወሰድ የሚችል ብድር ወይም እያደጉ ያሉ አገራትን ለመደገፍ የሚቀመጡ የትላልቅ ድርጁቶች የድጋፍ ገንዘብ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ዕቅዳዊ ወይም ሥልታዊ ልግሥና ሙሉ በሙሉ እንግዳ ወይም አዲስ ነገር አይደለም፤ ነገር ግን ዕድሎችን በአግባቡ መጠቀም ፈልገን ብንጸልይም ያሉትን ዕምቅ ኀይሎች መመልከት አልጀመርንም።

ባለ ጠጎች ብንሆን፣ የቱንም ያህል ውስብስብ ነገሮች ቢኖሩም ወይም የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ብንሆንም የጳውሎስ መመሪያ ይመለከተናል ወይም ለሁላችንም ይዛመዳል። ምናልባት እንደ ክርስቲያኖች ሕይወታችሁን በጥንቃቄ የምትመሩ ልትሆኑ ትችላላችሁ፤ ይህ ትልቅ ነገር ነው። ነገር ግን ጥቂት ጊዜ ወስደን ይበልጥ በዕቅድ የምንመራ ወይም ሥልታዊ ስለ መሆን ማሰብ ተገቢ ነው።

ያገኘነውን ዕድል/አጋጣሚ በሚገባ ከመጠቀማችን በፊት ዕድሉን በሚገባ መረዳት ይኖርብናል። በብዙ ሥራዎች በመጠመድ እና በመባከን ወደ እኛ የሚመጣውን ዕድል ሙሉ በሙሉ ሳናስተውል ማሳለፍ ያልተለመደ ነገር አይደለም። ጥቂት ደቂቃዎች ወስዳችሁ በእያንዳንዱ ቀን ማብቂያ ላይ እግዚአብሔር የቀናችንን ውሎ በተመለከተ ማብራሪያ ወይም አስተያየት እየሰጠን እንደ ሆነ አስቡ፤ በዚህ ወቅት እግዚአብሔር በቀኑ ውስጥ ወደ እኛ ያመጣቸውን፣ በአግባቡ ተረድተን ያልተጠቀምንባቸውን ዕድች እንድናስተውል እያደረገን እንደ ሆነ አስቡ። ላልተጠቀምንባቸው ዕድሎች በእንዲህ ዓይነት መልኩ በየዕለቱ ብንጠየቅባቸው በቀጣይነት ወደ እኛ የሚመጡትን ዕድሎች ይበልጥ በንቃት እንጠቀምባቸው ነበር።

አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም ብላችሁ ወደ ኋላ በመመለስ ያለፈውን ሳምንት አስቡ። “የለጋስነት ዕድሎች” መነጽርን በመጠቀም ያመለጣችሁን ዕድሎች ወደ ኋላ ዞር ብላችሁ ማስታወስ ትችሉ ይሆን? (እኔም ይህን መልመጃ ሠርቻለሁ፤ አዎ፣ ከስድስት ሰዓት በፊት ትልቅ ዕድል አምልጦኛል። በእርግጥ በእግዚአብሔር ጸጋ ቶሎ ሳይረፍድ ላስተካክለው እችል ይሆናል።)

ልክ እንደ እኔው ያመለጣችሁን ዕድሎች ማየት ብትችሉ እንኳን ተስፋ እንዳትቆርጡ። ማድረግ የምትችሉት ነገር ከሆነ ሳይረፍድ አሁኑን ፈጽሙ፤ ካልሆነ ግን ካለፈው ትምህርት ወስዳችሁ ለወደ ፊቱ ለመጠቀም እንድትችሉ የጸሎታችሁ አካል አድርጉት። በልግስና ለመስጠት ዕድሎችን በአግባቡ የመገንዘብን ልምድ ማዳበር የመጀመሪያው ደረጃ ነው። በእርግጥ ዕድሎች ከሰማይ ዱብ እንዲሉልን መጠበቅ የለብንም - እኛ ራሳችን በፈለግነው ጊዜ ዕድሎችን መፍጠር እንችላለን።

ይሁን እንጂ ዕድሎችን ለይቶ መገንዘብ የመጀመሪያው ደረጃ ነው። አስደሳቹ ክፍል በቀጣይነት የሚመጣው ነገር ነው፤ የተረዳነውን ዕድል ምን እናደርገዋለን? የተወሰኑ አማራጮች አሉን። ወደ እኛ የመጣውን ዕድል ሆነ ብለን ቸል ማለት እንችላለን። በአግባቡ አስተውለን ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን። ወይም ደግሞ በዕቅድ፣ ሥልታዊ በሆነ መልኩ ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን።

**ሙግት ለቀን አምስት**

እኛን በሚሞግተን መልኩ ሦስት ቀላል መመሪያዎችን እጠቁማለሁ፤ እነዚህ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ልንለማመዳቸው የሚገቡ ሲሆን ጳውሎስ የሚናገረውን ተግባራዊ እንድናደርግም ያግዙናል።

**እነሆ ሙግታችሁ፡-**

- 2ኛ ቆሮንቶስ 9÷6-12 ን አንብቡ።
- የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማገልገል ጊዜያችሁን፣ ችሎታችሁን እና ገንዘባችሁን ለመስጠት እግዚአብሔር አዲስ ዕድል እንዲገልጥላችሁ ወይም እንዲያሳያችሁ ጸልዩ። በመንገዶቻችሁ ላይ የሚያስቀምጣቸውን ዕድሎች መመልከት እንድትችሉ እግዚአብሔር ዓይኖቻችሁን እንዲከፍት በየዕለቱ ጸልዩ። በፊታችሁ ያለውን አንድ ዕድል መመልከት ከቻላችሁ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ በመቀጠል እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባችሁ ቆም ብላችሁ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ ጠይቁ። አንዳንድ ጊዜ ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት በቂ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሥልታዊ በሆነ መልኩ አቅዶ ምላሽ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል። በዓመት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን፣ ምሪቱን ለመጠየቅ እና በትክክል ድምጹን ለመስማት የተወሰነ ጊዜ ሊኖራችሁ ይገባል። በዚህ ለእርሱ በለያችሁት ጊዜ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ዕድሎች በሚገባ እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ አስቡ፤ እንዲሁም አጥብቃችሁ ጸልዩ። ይህ በስንፍና የተያዛችሁ ሳይሆን ንቁ ባለ ዐደራዎች እንድትሆኑ ያደርጋችኋል!
- ላገኛችሁት አዲስ ዕድል ሳትዘገዩ ወዲያውኑ ምላሽ ስጡ፤ አጋጣሚው ወይም ዕድሉ ሲገኝ ለጋስነታችንን ወዲያውኑ በተግባር መግለጽ ይጠበቅብናል። እነዚህን ነጥቦች የምታካፍሉት (የምታወሩት) አንድ ጓደኛ ወይም ትንሽ ቡድን ይኑራችሁ።

በሚቀጥለው ጊዜ ልግስናችሁን በተግባር የምታሳዩበት ዕድል ሲገጥማችሁ ዕድሉ “ዓሣ የመስጠት” ወይስ “ስለ ዓሣ አጠማመድ የምታስተምሩበት” ዕድል መሆኑን በጥንቃቄ መርምሩ። ዕድል ስላገኛችሁ ብቻ የሆነ ነገር አታድርጉ፤ ያገኛችሁትን ዕድል ተጠቅማችሁ የተሻለ ነገር አድርጉ! ይህንንም ለእግዚአብሔር መንግሥት ስትሉ አድርጉ!

ዛሬ ከእግዚአብሔር የተቀበልኩትን መልሼ በመስጠት ልግስናዬን በተግባር ለመግለጽ አዲስ ዕድል እፈልጋለሁ፤ እግዚአብሔር እንደ መራኝ ተገቢውን ምላሽ እሰጣለሁ።

# ቀን ስድስት

## የልግስና “ሮለር ኮስተር” (Roller Coaster): የአርባ ቀናት ልግስና

BY PASTOR RONY MADRID (GUATEMALA)

---

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍል ምንባብ**

“እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፣ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፣ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፣ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራህንስ ለተራበ ትቈርስ ዘንድ፣ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፣ የተራቈተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፣ ከሥጋ ዘምድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን?” (ኢሳይያስ 58፥6-7)

**ትምህርት**

በድንብ ለመጫወትና ለመደሰት ከፈለጋችሁ የልግሥና “ሮለር ኮስተር” ማሽከርከር አለባችሁ። እኔ የምኖረው ብዙ ፈተናዎች በሙሉባት በጓቴማላ አገር ነው። ምናልባት ትልቁ ፈተና ጌታ የሚያየውን ማየት መቻል እና እርሱ የሚፈልገውን ማድረግ ነው። በዚህ ትልቅ ድኅነት አለ፤ እዚህ የሚወለዱ ሁሉ ድኅነትን በአከባቢው የመወለድ አካል መሆኑን መቀበል ተምረዋል። እኔ ”ሪል ላይፍ” (REAL LIFE) የምትባል ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነኝ፤ እናም በኢሳይያስ 58 በሚገኙ ቁጥሮች እግዚአብሔር ችግረኞችን እንድረዳ ልቤን አነቃቃ። በዚህ ክፍለ ምንባብ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲህ ይላል፤ “ድኾችን ለመርዳት ራሳችሁን ካልሰጣችሁ ሃይማኖታችሁ በፍጹም አያስደንቀኝም።”

የእግዚአብሔርን ሐሳብ ከተገነዘብን በኋላ “INICIATIVA 58” የሚል እንቅስቃሴ ለመጀመር እና የ40 ቀናት ልግስና ተብሎ የሚጠራ አገር-ዐቀፍ ዘመቻ ለማካሄድ ወሰንን። ቤተ ክርስቲያንን እና በጓቴማላ የሚገኙትን ክርስቲያኖች በሙሉ ስለ መስጠት በረከት ማስተማር እና የእግዚአብሔርን ፍቅር በአገሪቷ ለሚገኙ ችግረኞች ሁሉ ማሳየት ፈለግን። ራእያችንን የምናካፍልበት እና መጋቢዎች በጥሞና ጊዜያት ስለ መስጠት እንዲያስተምሩ፣ እንዲሁም ለጥሞና ጊዜ የተዘጋጀውን ጥናት ቤተ ሰቦች ሁሉ እንዲያነቡ እንዲጋብዙ የምንሞግትበት ጊዜ ነበረን። በ40 ቀናቱ ማብቂያ ላይ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በፊት ሰብስበው የማያውቁትን ትልቅ ስጦታ እንዲሰበስቡ ጠየቅን። ይህንን በንጹሕ ልብና ቅንነት ለማከናወን ቤተ ክርስቲያን የምትሰበስበው ስጦታ ሙሉ በሙሉ ችግረኞችን ለመርዳት እንደሚውል ተገለጸ። ከአንድ መቶ በላይ አብያተ ክርስቲያናት፣ ዲኖሚኔሽኖች፣ አገልግሎቶች፣ በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ እና የተለያዩ ቡድኖ ች በዚህ ለአገራችን በሚደረግ የ40 ቀናት ልግስና መርሐ ግብር ለመሳተፍ ወሰኑ።

በመካከላችን የተገለጠውን ለጋስነት ከሚያሳዩ ምሳሌዎች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡-
• አንዲት ወጣት ልጅ በጕጕት ለሚጠበቀው እና በላቲን አሜሪካ አንድ ሰው 15 ዓመት ሲሞላው በከፍተኛ ወጪ ለሚከበረው በዓል (QUINCEAÑERA CELEBRATION) የተጠራቀመላትን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለችግረኞች ቤት መሥሪያ እንዲሰጥ አበቷን ጠየቀች።
• የልጆቻቸውን ልጆች በሙሉ ወደ “DISNEY WORLD” በመውሰድ ለማዝናናት ያሰቡ ጥንድ አያቶች ገንዘብ ያጠራቅሙ ነበር። የ40 ቀናት ዘመቻ ማጠናቀቂያ ላይ እነዚህ ልጆች ወደ አያቶቻቸው መጥተው እነርሱን ለማዝናናት ያጠራቀሙትን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለድኾች ቤት መሥሪያ እንዲሰጡ ጠየቁ። ከልጆቹ መካከል የስምንት ዓመት ልጅ የነበረው አንዱ ልጁ ለአያቶቹ እንዲህ አለ፤ “አያቴ፣ እግዚአብሔር አንድ ቀን ወደ DISNEY WORLD እንድንሄድ ከፈለገ ሌላ መንገድ ያዘጋጅልናል። እነዚህ ችግረኛ ቤተ ሰቦች ግን አሁን የእኛ እገዛ ያስፈልጋቸዋል።”
• አንድ ክርስቲያን ነጋዴ ሠራተኞቹ በሙሉ ለችግረኞች ቤት መሥሪያ ገንዘብ እንዲሰጡ በማነሣሣት ሞገታቸው። እነርሱ የሚያዋጡትን የገንዘብ መጠን እጥፍ አድርጎ እንደሚሰጥ ነገራቸው። ሠራተኞቹ 15,000 ዶላር አዋጡ፤ እርሱም 15,000 ጨመረበት - በጋራ የእነርሱ ድርጅት 20 ቤቶችን ለችግረኞች መሥራት ችሏል።

አርባ ቀናቱ ሲጠናቀቁ የ20,000 ዶላር ስጦታ ወይም የ40,000 ወይም የ60,000 ስጦታ አልተቀበልንም። የተሰጡት ስጦታዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ሲቆጠሩ በጠቅላላ ያገኘነው 469,000 ዶላር ነበር፤ ይህም 312 ቤቶችን ለመገንባት በቂ ነበር።

ይህ ቤተ ክርስትያናችን በታሪኳ በአንድ ጊዜ የሰበሰበችው ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ነው። በእነዚህ 40 ቀናት እግዚአብሔር በእኛ እና በእኛ በኩል አልፎ በሌሎች ስላደረገው ሁሉ እጅግ እናመሰግነዋለን።

**ሙግት ለቀን ስድስት**

ለጋስ መሆን አስደሳች ነው። በዚህ አጭር የጥሞና ጊዜ በጕዞአችን ያየናቸውን ተዓምራት ሁሉ መናገር አልችልም። ማድረግ የምችለው አንድ ነገር ቢኖር እግዚአብሔርን ወደምንታዘዝበት እና ልዕለ-ተፈጥሮአዊ መግቦቱን ወደምናይበት ወደዚህ የልግስና “ሮለር ኮስተር” እናንተን መጋበዝ ነው።
እነሆ ሙግታችሁ፡-

• ኢሳይያስ 58፥5-7 ን አንብቡ።
• እንድትለግሱ አዲስ ራእይ እንዲሰጣችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ። ከእግዚአብሔር ስሙ። ልትለግሱ ወደሚገባችሁ አንድ ሥፍራ ወይም ሁኔታ እግዚአብሔር እንዲመራችሁ ልባችሁን ከፍታችሁ ጸልዩ። ምናልባት ሐሳቡን ለተወሰነ ጊዜ በልባችሁ ውስጥ አስቀምጦት ይሆናል፤ በእምነት ለመንቀሳቀስ ግን ጊዜው አሁን ነው። እግዚአብሔር እንድታደርጉ የሚፈልገውን ነገር በትክክል እስከትረዱ ድረስ መጸለያችሁን አታቋርጡ።
• እግዚአብሔር በልባችሁ ለሚያስቀምጠው ምላሽ ስጡ፤ በእርሱ ለመሞገት እና ለመባረክ ተዘጋጁ። ለጋስ በመሆን ኀላፊነት ውሰዱ፤ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ሁኑ። “ሮለር ኮስተርን” በማሽከርከር የእናንተ ድርሻ ይህ ነው። እግዚአብሔር በልባችሁ ውስጥ ያስቀመጠውን በእምነት ታዘዙ። በእርግጥም ከእርሱ ዘንድ የመጣ ከሆነ በእርሱ መታመን እና መበርታት ይጠይቃል። ወደ ኋላ የምታስቀሩት ነገር አይኑር - እርሱ እንድትፈጽሙት በልባችሁ ያስቀመጠውን ነገር ተነሡና ፈጽሙ። እርሱ በምን መልኩ እንደሚመራችሁ እና እንደሚያዘጋጅላችሁ ተመልከቱ። እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን እንደሚያዘጋጅላችሁ ጠብቁ፤ እንዲሁም ለመደነቅ ተዘጋጁ። የእናንተን ልግስና እንዴት እንደሚያበዛው እና እንደውም ይበልጥ ወደ መስጠት ደረጃ እንደሚያሳድጋችሁ ወይም እንደሚጠራችሁ ተመልከቱ። ይህ “ሮለር ኮስተር” እንደ ሆነ አስታውሱ። በማሽከርከሩ እንደሰት!

ዛሬ ኀላፊነት በመውሰድ ወይም ዋጋ ለመክፈል በመዘጋጀት እግዚአብሔር እንደ መራኝ በአዲስ መልክ የመለገስ ተግባር እፈጽማለሁ።

# ቀን ሰባት

## የልግስና ግብ፤ የተለወጠ ሕይወት መኖር

BY DENNIS FAST (UNITED STATES)

---

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍል ምንባብ**

“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡” (ዮሐንስ 3÷16)

**ትምህርት**

በአንድ ዓረፍተ ነገር የተቀመጠው ዮሐንስ 3÷16 “የምሥራች” ብለን የምንጠራው ወይም የወንጌል እምብርት ነው፡፡ ይህ ለእምነታችን መሠረት እና እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ያለው የማዳን ዕቅድ ዓይነተኛ መገለጫ ነው፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የሰጠው ከዚህ የፍቅር ልቡ ነው፤ በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት ያገኛሉ፡፡ ይህ ቁጥር ኢየሱስ ከሕግ መምህሩ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ንግግር ቀጣይ ክፍል ወይስ ዮሐንስ (ጸሐፊው) በንግግሩ ላይ ተመስርቶ ያቀረበው ማብራሪያ የሚለው ምሁራንን ለረጅም ጊዜ ሲያከራክር የቆየ ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተከራክረን የትኛውንም አቋም ብንይዝ የያዝነው አቋም (አመለካከታችን) በዚህ ቁጥር የተገለጠውን እውነት ያህል ጠቃሚ አይደለም፡፡ ይህ የእግዚአብሔርን ባሕርይ እና ለዓለም ያለውን ፍቅር በጥሩ መልኩ የሚገልጽ ወይስ ስለ እግዚአብሔር አንድ ነገር ከሚያሳዩ ክፍለ ምንባባት መካከል አንዱ ነው?

የምናምነው ከሆነ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅዱ ጥልቅ መገለጫ ነው፤ ቀለል ብሎ ቢቀርብም ክርስቶስ ወደዚህቹ ምድር መጥቶ መታወጅ ከጀመረበት ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ጀምሮ ያመኑትን ሁሉ ሕይወት እየለወጠ ያለ እውነት ነው፡፡ ምናልባት፣ “ይህን ከልግስና ጋር ምን ያገናኘዋል?” ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሼ  “ሁሉም ነገር!” የሚል ነው፡፡ ጎርደን ማክዶናልድ ስለ ልግስና በጻፈው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፤ “በልግስና የሚሰጥ (ለጋስ) ሰው መሆን ከፈለጋችሁ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምንባብ (ዮሐንስ 3÷16) በቅርበት ልታውቁ ይገባል፡፡ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ አስቀድሞ ያላደረገልንን ነገር እንድናደርግለት እንደማይጠይቀን ያስታውሰናል፡፡ የመጀመሪያው ለጋስ/ሰጪ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ የልግስናን የመጨረሻውን ምሳሌ/ዓርዐያ ሰጥቶናል፤ እናም መጽሐፍ ቅዱስን የሚቀበሉ ሰዎች ሁሉ እርሱ የሰጠውን ፈለግ እንዲከተሉ ጥሪ ያደርጋል፡፡”

ልግስናን የምንከታተልበት ይህ ሳምንት ወደ መገባደድ እየመጣ ባለበት በዚህ ወቅት በአንድ ሐሳብ እሞግታችኋለሁ፤ ይኸውም፣ መስጠት ማለት መንፈሳዊ መሆን (እግዚአብሔርን መምሰል) ማለት ነው፡፡ አንዳንዶች እንደውም ከዚህ አለፍ ብለው ከዮሐንስ 3÷16 አኳያ ስንሰጥ ይበልጥ እግዚአብሔርን እንደምንመስል ይናገራሉ፡፡ አያችሁ፤ ትክክለኛው የለጋስነት ግቡ ቤተ ክርስቲያን እንድትበለጽግ፣ ለበጀቷ የሚያስፈልጋት ገንዘብ እንዲሟላ/እንዲሰበሰብ ወይም ሕንጻ መሥራት እንድትችል ማገዝ አይደለም፡፡ የልግስና ግቡ በመስጠት እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘሁት በምላሹ የእኔ መባረክ አይደለም፡፡ የልግስና የመጨረሻው ግብ የግለ ሰብ ለውጥ (መለወጥ) ነው፡፡

ይህ በመስጠት እና እግዚአብሔርን በመምሰል መካከል ያለውን ግንኙነት እንድታዩ ይረዳል?

ለውጣችን ጥልቅ የሆነውን ያህል በባሕርይ፣ በአስተሳሰብ እና በተግባር እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እንቀርባለን፡፡ ለውጥ የሰውነት ቆዳ ላይ የሚታይ ወይም ውጫዊ አይደለም፤ ለውጥ ከውስጥ ጀምሮ እስከ ውጪ ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ የሚጀምረው እና የሚያድገው ከልብ ነው፤ ይበልጥ አዳኛችንን ከሚመስል ልብ ማለት ነው፡፡

ከድኻ ቤተ ሰብ የሆነ አንድ ወጣት ልጅ አስታውሳለሁ፤ ይህ ወጣት ልጅ ለሠፊ/ለትልቅ ቤተ ሰቡ በቂ ያልሆነ አነስተኛ ምግብና ሸቀጣ ሸቀጦች በቦርሳው ይዞ ወደ ቤት በመጓዝ ላይ ነበር፡፡ በጣም በተጨናነቀ መንገድ ወደ ቤቱ እየተጓዘ በነበረበት ወቅት አየሩ ብርዳማና ሰዓቱም ከመሄዱ የተነሣ እየጨላለመም ነበር፤ ይህ ልጅ እየተራመደ ሳለ ድንገት ቦርሳው ተቀደደ፤ በውስጡ የነበረው ዕቃ ሁሉ በመንገደኞች መረማመጃ ላይ ተበታተነ፡፡ በችኮላ ሲጓዙ የነበሩ አብዛኛዎቹ መንገደኞች የተበታተኑትን ዕቃዎች እያዩና በእግሮቻቸው ወደ ጎን እያደረጉ በፍጥነት ማለፋቸውን ቀጠሉ፤ ከመንገደኞቹ አንዱ ግን ለዚህ ወጣት ልጅ እጅግ በጣም አዘነ፡፡ ይህ ሰው አጎንብሶ የተበታተኑትን ዕቃዎች በመሰብሰብ፣ የተሰበረውን በማጽዳት እና የሰበሰበውን በቦርሳው እንደ ገና በማስገባት ወጣቱን ልጅ አገዘ፡፡ መሰብሰቡንና በቦርሳ ማስገባቱን በጋራ ወደ ማጠናቀቅ ሲመጡ ትንሹ ልጅ ዕንባ በጉንጮቹ ላይ እየፈሰሱ ያገዘውን ሰው ቀና ብሎ እያየ የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቀው፤ “ጌታዬ፣ አንተ ኢየሱስ ነህ?”

አዎ! ለጋስ ስንሆን፣ ለሌሎች ስንሰጥ ይበልጥ እግዚአብሔርን እንመስላለን፡፡ ጋንዲ በአንድ ወቅት ተከታዮቹን እንዲህ በማለት ሞግቷል፤ “ዓለምን ለመለወጥ ታላቁ መንገድ ራሳችን በዓለም ልናየው የምንመኘውን ለውጥ መሆን ነው፡፡” ለውጥ ሁኑ! እግዚአብሔር አምላክ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ልባችሁን እና አእምሮአችሁን የልጁን መልክ እንድትመስሉ ይለውጥ፡፡ ይህ ለውጥ ልግስናን ያካትታል፤ ወደ አዲስ ዓይነት ለጋስነት ይመራችኋል፡፡ ዛሬ እግዚአብሔር እነዚህን ሰባት ቀናት በመጠቀም ልግስናን የሕይወታችህ ዘይቤ (የኑሮአችን አካል) እንዲያደርጋቸው እንጸልያለን፡፡

**ሙግት ለቀን ሰባት**

ምናልባት በቤተ ክርስቲያናችሁ ወይም በሌሎች ድርጅቶች አነሳሽነት አማካኝነት በበርካታ “የባለ ዐደራነት ዘመቻ” ላይ ተሳትፋችሁ ይሆናል፡፡ እነዚያ በተወሰኑ ጊዜያት እግዚአብሔር በተለየ መልኩ ሲሠራ የተመለከታችሁበት ድንቅ ክፍለ ጊዜያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ የሰባት ቀናት ሙግት አንድ ጊዜ ከመስጠት ልምምድ ባለፈ ሕይወትን በአዲስ መልክ የመመልከት ፍሬ ቢያፈራስ? ለእናንተ ያለኝ ጸሎት ይህ ነው፤ ሰባቱ ቀናት ወደ ሰባት ሳምንታት፣ ብሎም ወደ ሕይወት ዘመን ተመንዝረው እግዚአብሔር ለሠራላችሁ ነገር ሳያቋርጥ የሚፈስ ምስጋና ከውስጣችሁ ይፈልቅ ዘንድ ጸሎቴ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚያስችላችሁ ያላችሁ የገንዘብ መጠን አይደለም፡፡ ዕለት በዕለት እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ እንጂ፡፡

**እነሆ ሙግታችሁ፡-**

- ሮሜ 12÷1-2 ን አንብቡ፡፡
- ይህን ዓለም የመሰላችሁባቸውን መንገዶች እንዲገልጥላችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ፤ በልባችሁ መታደስ ትለወጡ ዘንድ እንዲረዳችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ፡፡
- በኢየሱስ በማመን ወደ ድነት የመጣችሁበትን ጊዜ አስቡ፤ ያገኛችሁትን የድነት ሥጦታ ተዛምዶዎች እያሰባችሁ ጥቂት ደቂቃዎች ወስዳችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ (ዮሐንስ 3÷16)፡፡
- አንድ ገጽ ወረቀት በማውጣት የሚከተሉትን በዝርዝር በመጻፍ ምላሽ ስጡ፡-
  1. ዛሬ እግዚአብሔርን የምታመሰግኑባቸውን አሥር ዐብይ ጉዳዮች ጻፉ፡፡

2. ስታስቡት ይበልጥ የሚያሳስባችሁ ወይም የሚያስጨንቁአችሁ ነገሮች ምን ምን ናቸው (1ኛ ጴጥሮስ 5÷7 ን አስቡ፤ “እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።”
3. በዚህ ባለፈው ሳምንት ውስጥ ለማከናወን ቃል የገባችሁትን ነገሮች ሁሉ ጻፉ።
4. ራሳችሁን እና ያላችሁን ሁሉ እንደ ገና ለእግዚአብሔር የምትሰጡበት አጭሩ ጸሎት አድርጉ።

ዛሬ እግዚአብሔር በሕይወቴ ውስጥ ላስቀመጣቸው መልካም ነገሮች ሁሉ አመሰግነዋለሁ፤ ወድጄና ፈቅጄ በየዕለቱ እከተለዋለሁ፤ እንዲሁም በአእምሮዬ መታደስ መለወጤን እቀጥላለሁ።

## ADDITIONAL STEWARDSHIP RESOURCES

MB Foundation is available to help you on your stewardship journey towards faithfulness. May we be more than simply good financial managers in solid financial shape, but rather strive to live God-honoring lifestyles; so that the owner and creator of the universe, will one day say, “well done, good and faithful trustee.” Resources available include:

- Giving Meaning to Money Devotional (monthly email). Our free monthly stewardship devotional.
- Money. Purpose. Joy. A seven-week study by Matt Bell that fills in the missing pieces of the financial puzzle, designed primarily for use by church small groups or as a video-based workshop.
- The God Pocket. Educational materials to help your congregation make giving personal!
- Budget Resources. Budget resources to assist you in managing God’s resources.

These resources and more are available at www.mbfoundation.com/championingstewardship.

## MB FOUNDATION SERVICES

**Planned Giving Services –** There are many ways to give and MB Foundation can help you achieve your charitable goals that benefit you and the ministries you love.

**Fund Management –** MB Foundation manages over $180 million in total assets. As a fiduciary of these assets we are committed to stewarding funds with excellence.

**Championing Stewardship –** Preaching, workshops and resources are available to encourage individuals and churches toward a God-honoring use of their resources.

**Loan Program –** Financing is available to ministries for property purchases, building projects and capital improvements. We also offer home loans to pastors.

**Investment Certificates –** Earn an excellent rate of return AND participate in the MB community by providing capital for our Loan Program.

***Contact us at 1.800.551.1547 or visit www.mbfoundation.com for more information.***

## KEY CONTRIBUTORS

**Forrest Jenan**, *Lead Pastor at Neighborhood Church*

Pastor Forrest serves as lead pastor of Neighborhood Church in Visalia, California. Forrest wrote the generosity challenge sermon outline.

**Endashaw Negash**, *Translator*

Brother Endashaw is involved in teaching and preaching in different theological colleges and churches in Ethiopia. He has a passion for spreading the Gospel and encouraging people to be involved in generosity.

**Dennis R. Fast**, *Interim Pastor at Hope Kingsburg Church*

Dennis is a long-time pastor in the Midwest and the West Coast and served as Interim Pacific District Conference Minister. Dennis edited the generosity challenge materials.

**Jon C. Wiebe**, *President & CEO of MB Foundation*

Jon has been providing leadership to the Foundation since 1996 and has a heart for helping individuals and ministries honor God with their finances. Jon spearheaded and coordinated the generosity challenge materials and served as editor.

MB FOUNDATION
Giving Meaning to Money®

200 EAST D ST, HILLSBORO, KS 67063
P 620.947.3151   F 620.947.3266   TOLL FREE 800.551.1547

www.mbfoundation.com